# መልካችን፣ ልካችን በደማቁ የሰፈረበት ውድ ገጻችን ነው!!

**ዮናስ 03/19/14**

"ተፈጥሮ ሀገራት ላሰመሩት ድንበር አትገዛም" የሚለውን ሀሳብ ያስቀደምኩት ከተፈጥሮ ፀጋዎቻችን መካከል ወንዝን ሊያውም ዓባይን እና ታላቁን የህዳሴ ግድብ በተመለከተ ከተፋሰሱ ሃገራት በተለየ ጽንፍ ቆማ ሰሚ የሌለውን ጩኸት በማሰማት ላይ ያለችውን ግብፅ በተመለከተ ለማነሳው ሃሳብ ጥሩ ማሳያ ስለሆነልኝ ነው - (Nature does not respect man-made political borders) በሚል፡፡

ልክ ነው፤ "ተፈጥሮ ሃገራት ላሰመሩት ድንበር አትገዛም" እንደማትገዛ ደግሞ የተፈጥሮ አካል ከሆነው ወንዝ ጋር የተያያዙ ሁነኛ ማሳያዎችን መጀመሪያ እናስቀድም፡፡

በዓለማችን ከ300 በላይ የሚሆኑ ወንዞች ድንበር ተሻጋሪ ናቸው፤ በህንድና በባንግላዴሽ መካከል ብቻ 54 ወንዞች ድንበር ተሻግረው ይፈሳሉ፡፡ በ1978 በዓለማችን 214 ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች እንደነበሩ የሚጠቁሙ መረጃዎች በ2002 ደግሞ 263 መድረሳቸውን ያመለክታሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 145 ሃገራት ድንበራቸውን የከለሉት በድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ነው፡፡ ላለፉት 50 ዓመታት 1831 ያህል ስምምነቶችና ግጭቶች በእነዚህ ወንዞች ዙሪያ መከሰታቸውና ከ200 በላይ የትብብር ስምምነቶች መፈረማቸውም በታሪክ መዝገብ ላይ የሰፈረ የዓለማችን እውነት ነው፡፡

ዋናው ጉዳይና ከዓባይ ጋር የሚያያዝልኝ ዓለማዊ እውነት ግን ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ዋናው ነጥብ የዓለማችን 40 ከመቶ የሚሆን ህዝብ ህይወቱን ከድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ጋር በማቆራኘቱና ከላይ በተጠቀሱት እውነታዎች ሳቢያ እነዚህ ወንዞች የዘወትር አጀንዳ እንደሆኑ የመቆየታቸው እውነታ ነው፡፡ ምክንያቶቻቸውን በማህበራዊና በፖለቲካዊ አጀንዳዎች ሥር ዘርዝረው ሃገራት በተደጋጋሚ ይስማማሉም፤ ይጋጫሉም፡፡ በተለይ ወንዞችን ለልማት ለማዋል የሚደረጉት ሙከራዎች በአብዛኛው በውዝግብ የተሞሉ ናቸው፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ የእነዚህን ወንዞች ባህሪያትና እውነታዎች ወክለው በምሳሌነት መጠቀስ ከሚችሉ ወንዞች መካከል ናይል የመጀመሪያው ነው፡፡ ከርዝመቱ፣ ከአፍሪካዊነቱ እና ከአጠቃቀሙ ወለፈንዷዊነት፣ ከተፈጥሮአዊ ተፋሰሱ እና

ከታሪክ ሽኩቻዎቹ የተሰበሰቡ እውነታዎች የናይልን ዓለም አቀፋዊ ቀለም ደማቅ ያደርጉታል፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሃገራችን ኢትዮጵያን ጨምሮ የተፋሰሱ ሃገራት ለወንዙ ዓለም አቀፋዊ ቀለመ ደማቅነት ያበረከቱት ድርሻ ቢኖር "ይኼን ያህል ድርሻ ያላቸው!"፣ "የናይል ምንጭ"፣ "የተፋሰሱ ሃገራት!" ወዘተ ከሚሉ ስሞችና ሐረጋት የዘለለ አልነበረም፡፡ ምሥጋና ለእልህ አስጨራሹ የዲፕሎማሲ እና የልማት ሥራዎች ይግባና፤ ዛሬ ኢትዮጵያ ዓባይዋን የህዳሴዋ መገለጫ ለማድረግ ወገቧን ምዕራፍ ገልጣ እየተጓዘች ነው፡፡ እስካሁንም በከፍተኛ ህዝባዊ ርብርቦሽ እየተጓዘ በመቀላጠፍ ላይ ይገኛል፡፡ የዚህ ከታሪክም በላይ የሆነ እውነት መፈጠር ደግሞ ፍካሬው የበዛ ገድል ነው፡፡

ነገር ግን እንደ አብዛኛው የዓላማችን ግዙፍ የውኃ ኃይል ማመንጫ ግድቦች እና የናይል ጉዳይ እንደመሆኑ ታለቁ የህዳሴ ግድብ ዓለማቀፋዊ መልክ የያዙ ፈተናዎችን መጋፈጡ አይቀሬ ነው፡፡ እየተጋፈጠም ነው፡፡ ታዲያ ፈተናዎቹ ከሃገር ሃገር ክብደታቸው ይለያይ ይሆናል እንጂ የመከሰታቸው ነገር የማይካድ ወይም "ለምን መጣ?"› የማይባል ነው፡፡ ብዙ ሃገራት እነዚህን ፈተናዎች ተጋፍጠው ዓላማቸውን ከግብ አድርሰዋል፡፡ ዋናው ሃገራዊ መሠረታቸውን መጠበቃቸው፣ በቁርጠኛ ፖለቲካዊ ውሣኔ መታገዛቸው፣ በህዝባዊ የእኔነት ስሜት መደገፋቸው ወዘተ…ነው የፈተናዎቹን ክብደት የሚያቃልለው፡፡

ስለሆነም የእኛው ዓባይና የህዳሴው ግድብም በተመሳሳይ ፈተና ውስጥ ከገቡ ቢዘገይም ዛሬ ላይ ግን ፈተናው እየከረረ የመጣ ይመስላል፡፡ በእርግጥም ይህም ሆኖ የቆመና የተለወጠ ነገር የለም፡፡ ይልቁንም ቁጭቱ ሥራውን እያፋጠነው ነው፡፡ ከላይ በተመለከተው አግባብ ደግሞ የፈተናውን ምንጭ ለይቶና መፍትሄው ላይ አቋም ይዞ መጓዝ እንደ አብዛኛዎቹ ሃገራት የጀመርነውን ታሪክ በድል እንድናጠናቅቅ ይረዳናል፡፡ ለዚሁ  የመወያያ ሀሳብና የጋራ አቋም ደግሞ የግብፅን ናይል ተኮር ጠባጫሪ ሃገራዊ አቋም መነሻና ዛሬ ያለንበትን ደረጃ በመጠኑ ማየት ጠቃሚ ይሆናል፡፡ የህዳሴ ግድቡን በተመለከተ በጋራ ተጠቃሚነት ላይ ተመስርተን እንደምንሰራና ለዚሁም በርካታ ማረጋገጫዎችን እየሰጠን ባለንበት ሰዓት ግብፅ ጉዳዩን ከማጦዝ ተቆጥባ አታውቅም። ለምን ቢሉ ማስፈራራት፣ መዋሸት፣ ማምታታትና ጉዳይ ማንከባለል የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዋ ምሰሶ ስለሆነ። ለዚህም እኮ ነው እሥራኤላውያን ግብፆች ከሚናገሩት የሚያስቡትን መርምሩ የሚሉት። ግብፅ ውሸታም መሆኗ እና እኛ እውነተኛ መሆናችን በራሱ ግን አሸናፊ ያደርገናል ብለን ከተኛን ጨዋታው ፈረሰ፤ ዳቦው ተቆረሰ እንደሚሆን መጠራጠር የለብንም። በየመድረኩ አዳዲስ

አጀንዳ ይዘው በመምጣት ለሚታወቁቱ ግብፆች፣ ከቃላት በስተቀር የይዘት ልዩነት በሌለው የማምታቻ ሃሳባቸው ለሚታወቁቱ ግብፆች እኛም መዘየድ ይገባናል።

ለዚህ ደግሞ  መነሻው ያው የሆነና የተመለሰውን ጥያቄ መሠረት ያደረገ ግን ደግሞ መልኩን የቀየረውንና ከወደ ግብፅ የተሰማውን ሰሞንኛ ሰጣገባ በሚገባ ማጤን  ነው፡፡ ይህ እሰጥ አገባ የተሰማው ደግሞ ለግብፅ ባለሥልጣናት ቅርበት ያለው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የመረጃ እጥረት እንደሌለበት ከሚነገርለት አል ሞኒተር ከተሰኘ ድረገፅ ነው፤ ሌሎቹም የግብፅ ሚዲያዎች በእሰጣገባው የዘገባ ዘመቻ ተጠምደዋል፡፡

አል ሞኒተር የተባለው ድረ ገፅ ከህዳሴው ግድብ ጋር በተያያዘ ካሰፈረውና የበዙ የግብፅ መገናኛ ብዙኃኖች እየተቀባበሉ ካራገቡት ዘገባ መካከል ደግሞ ”ግብፅ ከህዳሴው ግድብ ጋር በተያያዘ ከኢትዮጵያ ጋር የገባቸውን ውዝግብ ለመፍታት የባህረ ሠላጤ ሀገሮች እንዲያደራድሯቸው ግልፅ የሆነ ጥያቄ ለማቅረብ እያሰበች ነው፡፡” የሚለው ዋናውና ቀዳሚው የመገናኛ ብዙኃን አጀንዳ ነው፡፡ ድርድሩ የሚከናወነው በሣውዲ ዐረቢያ መሪነት እንደሆነ የገለፀው አል ሞኒተር "የባህረ ሠላጤ ሀገራቱ የግብፅን አቋም እንዲደግፉ ተፈልጓል" ሲልም በዘገባው አመልክቷል፡፡

ግብፅ ሦስተኛ ወገን እንዲያደራድር ፍላጎት ያደረባት ካለፈው ጥር ወር (በታችኛው ተፋሰስ ሃገራት መካከል የነበረው ውይይት በግብፅ ግትር አቋም ውጤት አልባ ከሆነ በኋላ ለማለት ነው፡፡) አንስቶ የያዘችው ነገሩን ዓለም አቀፋዊ ለማድረግ እርምጃ አካል መሆኑን ጨምሮ የገለፀው አል ሞኒተር፡፡ ስማቸውን ያልገለፀው አንድ የግብፅ ባለሥልጣን ”ከኢትዮጵያ ጋር ግልፅ የሆነ ስምምነት ያልተደረሰበትን የህዳሴው ግድብ ግንባታ በተመለከተ የግብፅን ሥጋት የሚመረምርና የሚያብራራ ዘርዘር ያለ ሪፖርት እየተዘጋጀ ነው” እንዳሉትም በዘገባው አመልክቷል፡፡ የሚገርመው ደግሞ እንድታደራድራት ጥያቄ የቀረበላትን ሣውዲ በተመለከተ እኚህ ባለሥልጣን የሰጡት አስተያየት ነው፡፡

በድርድር መርህ ቀዳሚው የተደራዳሪዎቹ ሃገራት መልካም ፈቃድ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አደራዳሪ የሚሆነው አካል ደግሞ ከተደራዳሪዎቹ ያልወገነና ሚዛናዊ ዕይታ እንዲኖረው ግድ ይላል፡፡ ሆኖም ግን እኚህ ባለሥልጣን እንደተናገሩት ከሆነና አል ሞኒተር በዘገባው እንዳመለከተው ከሆነ ግብፅ የአሁኑን እርምጃ የጀመረችው የሣውዲ

ዐረቢያ እና የኤምሬትስ ባለሥልጣናት በብሄራዊ ጥቅሟ ላይ ተፅዕኖ በሚያስከትል ነገር ሁሉ ከጎኗ እንደሚቆሙ በቃል ከገለፁላት በኋላ ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፤ ከእነዚህና አደራዳሪ ከተባሉት ሃገራት ግብፅ ወደ 10 ነጥብ 7 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የገንዘብ እርዳታ ማግኘቷም በዘገባው ሰፍሯል፡፡ የአደራዳሪነት ቅሌት ይኼ ነው፡፡

የግብፅ ባለሥልጣናት ከሰሞኑ የህዳሴውን ግድብ አስመልክተው በዚህ ብቻ አላበቁም፡፡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯንም ከታችኛው ተፋሰስ ሀገራት መካከል አንዷ ወደሆነችው ታንዛኒያም ልካ ነበር፡፡ ዳሩ ግን የዓባይ ውኃ ለግብፅ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ በማብራራት ድጋፍሽን እንሻለን ያሏት ታንዛኒያ "ወንዙ የሚያልፍባቸው ሀገራት በሙሉ ውኃውን ለልማት የመጠቀም መብት አላቸው" በማለት ኩምሽሽ አድርጋ መልሳቸዋለች፡፡

ከላይ በተመለከተው አግባብ ግትር የሆነችው ግብፅ እንጂ ኢትዮጵያ እንዳልሆነች ግልጽ በሆነበት ሁኔታ የግብፅ የመስኖ ሚኒስትር ከሰሞኑ አሉ የተባለው ደግሞ አሳፋሪ ነው፡፡ የግብፅ የናይል ውኃ ድርሻ "ቀይ መስመር" በመሆኑ ማንም አቋርጦ እንዲያልፈው አትፈቅድም ሲሉ መናገራቸው ነው "ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮህል" የሚለውን የሃገሬ ብሂል አስታውሶ ያሳፈረኝ፡፡

ግብፅ በዚህ ብታበቃ ጥሩ፤ ግን አላበቃችም፡፡ ወደጣልያንም ጎራ ብላ ነበር አሉ፡፡ ለምን? ቢሉ፡፡ ግንባታውን የሚያከናውነው የሣሊኒ ኮንስትራክሽን አደብ እንዲገዛላት ለማድረግ፡፡ ዳሩ ግን ሣሊኒ አንድ ኩባንያ እንጂ ጣልያን እንዳልሆነ በመግለፅ በሽምግልና ከመፍታት ውጪ ጣልያን እንደ ሃገርና መንግሥት ሌላ ሚና እንደማይኖራት በመግለፅ እንግዶቹን በመጡበት እግራቸው መመለሷም ሰሞነኛው ዓባይን የተመለከተ እውነታ ነው፡፡

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ፣ የሱዳንና የግብፅ ባለሙያዎችን ጨምሮ ዓለም አቀፍ ኤክስፐርቶች የተካተቱበት ቡድን ያቀረበውን የጥናት ሪፖርት በመንተራስ ለቀጣይ ውይይት የሚረዱ ማዕቀፎችን ለማስቀመጥ በግብፅ፣ ሱዳንና ኢትዮጵያ መካከል የተደረገው የሦስት ጊዜያት ያህል ውይይት በግብፅ ተለዋዋጭ ሰበብ ከተበተነ በኋላ፤ ግብፅ የጭንቅላት ጨዋታና የግንባታ ሂደቱን በሚያደናቅፉ ሥልታዊ አካሄዶች ተጠምዳለች፤ የዓረቡን ዓለም በኢትዮጵያ ላይ ከማነሳሳት ጀምሮ ኢትዮጵያን ግራ ያጋቡልኛል ብላ ያሰበቻቸውን ሁሉ ድርጊቶች እየፈፀመች ነው፡፡ በዚህ ድንብርብሩ በወጣና መያዣ መጨበጫ በሌለው አስቀድሞ የከሸፈው ዲፕሎማሲያዊ መንገድ እንደተሳካላት በማራገብ የኢትዮጵያን አቋም

በአንድ በኩል በመፈተን ላይ ያለችው ግብፅ ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ አለኝ የምትላቸውን ካርታዎች ከመምዘዝ ባሻገር መሣሪያ ሸመታም ወደ ሩሲያ ጎራ ስለማለቷ በማስወራት ማስፈራራትንም አማራጭ አድርጋለች፡፡

ስለሆነም በዚህና ከላይ በተመለከተው አግባብ ህገ ወጥ የሆነው የግብፅ መወራጨት እንደ አንድ ፈተና ቢወሰድም አንድምታውንና ከኢትዮጵያውያን የሚጠበቀውን እዚህ ጋር ማውሳት ለተሻለ ድል ያበቃልና ወደዚያው እናምራ፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የህግና አስተዳደር ኮሌጅ ዲን ለሆኑትና የዓባይን ጉዳይ በተመለከተ መፅሀፍ ላሳተሙት ዶክተር ታደሰ ሪፖርተር የተሰኘው የሃገር ውስጥ ጋዜጣ የግብፅን የዲፕሎማሲያዊ ስኬት ጥሩንባ የተመለከተ ጥያቄ አቀረበላቸውና እንዲህ ሲሉ መልስ ሰጡ፡፡ በበርካታ ዓመታት ጠንካራ ሥራ የተመዘገበው የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ስኬት በግብፃውያን የጥቂት ሣምንታት ጉብኝት የሚቀለበስበት አንዳች ዓይነት ምክንያት እንደማይኖር የገለፁት ምሁር የቀረርቶውን መነሻ በተመለከተም ግብፅ በቅርቡ ከምታካሂደው ምርጫ ጋር እንደሚያያዝና የባለሥልጣናቱ ጉብኝት በኢትዮጵያ ላይ ተፅዕኖ ከመፍጠርና የግድቡን ግንባታ ከማስቆም ይልቅ የውስጥ ፖለቲካ አለመረጋጋቱን ለማብረድ ያለመ ነው ሲሉ ምሁራዊ ግምታቸውን ሰጥተዋል፡፡

የግብፃውያኑን የጣልያን ጉብኝት በተመለከተም አስተያየት የሰጡት ዶክተር ታደሰ ከአሜሪካ ጋር የነበራት ግንኙነት መቀዝቀዙን ተከትሎ የገንዘብ እርዳታ የሚያደርጉልኝ ሌሎች አማራጮች አሉኝ ለማለት የተደረገ እንደሆነ አንስተው "ከጦርነት ባሻገር ኢትዮጵያን ለማተራመስ ግብፅ ከፍተት ልታገኝ አይገባም፡፡" ሲሉ አስገንዝበዋል። በዚህ ረገድ የዴሞክራሲ ግንባታው፣ ሁሉን አቀፍ የልማት እንቅስቃሴው፣ ሁሉን አቀፍ የፖለቲካ ሥርዓት የመገንባት ሂደቱና ወዘተ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል" የሚል ምክራቸውንም ለግሰዋል፡፡

ሌላውና ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ህግ ትምህርት ቤት የዓለም አቀፍ ህግ መምህር የሆኑትና በዓባይ ጉዳይ ላይ የተለያዩ የምርምር ሥራዎችን ያሳተሙት ዶክተር ደረጀ ዘለቀም ጉዳዩን በተመለከተ ለሪፖርተር ጋዜጣ የሰጡት አስተያየት ነው፡፡

አሁን በሥልጣን ላይ ያለው የግብፅ አመራር በዴሞክራሲያዊ ሁኔታ በምርጫ ወደ ሥልጣን የመጡትን ፕሬዚዳንት ሙርሲ በመፈንቅለ መንግሥት በማስወገዱና በዚሁ መነሻ

ከአፍሪካ ህብረት ጭምር መወገዱን በማስታወስ ሰሞነኛውን የግብፅ መወራጨትና ”የስኬት” ጥሩንባ በተመለከተ ለጋዜጣው አስተያየት መስጠት የጀመሩት ዶክተር ደረጀ የባለሥልጣናቱን ጉብኝት ስኬታማ መሆንና አለመሆን ለመገምገም የጊዜው አጭርነት አስቸጋሪ እንደሚያደርገው ገልፀዋል፣ በምንም መንገድ ግን ግብፅ የጥቃት እርምጃ ልትፈፅም እንደማትችል ያላቸውን እምነት እንዲህ ገልፀውታል፡፡ ”በዓለም አቀፍ ህግ ጥቃት መፈፀም እ.ኤ.አ ከ1945 በኋላ የቀረ ነገር ነው፡፡ ልፈፅምም ብትል ግብፅ ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ አቅም የላትም፡፡ ነገር ግን ከዚህ ቀደም እንዳደረገችው ሁሉ በኢትዮ ሶማሊያና፣ በኢትዮ ኤርትራ እንደተፈፀመው ሁሉ ክፍተት ካገኘች በሌሎች ኃይሎች በኩል ኢትዮጵያን ለማዳከም ጥረት ማድረጓ አይቀርም” ብለዋል፡፡

ይህን ብለው ያላበቁት ዶክተር ደረጀ በተመሳሳይ እንደ ዶክተር ታደሰ ምክራቸውንም ጨምረው ለግሰዋል፡፡ እንዲህም ብለዋል፡፡ "ይሁንና ከላይ የተመለከተውን ክፍተት ለመድፈን የኢትዮጵያ መንግሥት ጠንካራ የሆነ መግባባት በወሣኝ ኃይሎች መካከል መፍጠር፣ የመልካም አስተዳደርና የኑሮ ውድነቱ ችግር ክፍተት እንዳይፈጥር ጥንቃቄ ማድረግ እንዲሁም ለብሄራዊ ጥቅም ከነችግራችንና ልዩነታችን በጋራ የመቆም ባህላችን ላይ ሊሰራ ይገባል” ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በእርግጥም የግብፅ መወራጨትና ‹‹የስኬት ጥሩንባ›› ከላይ ምሁሮቹ በገለፁት አግባብ የሚተረጎም እንጂ ፋይዳ የሌለው ጩኸት መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ደግሞ ምሁሮቹ ለኢትዮጵያ መንግሥት የለገሱት ምክርም እንዳለ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ያም ሆኖ ግን በምንም ተዓምር ግብፅ ስኬት አታመጣም ብሎ እጅን አጣጥፎ መቀመጥ ተገቢ አይደለም፡፡ በዓባይ ጉዳይ ላይ በግብፅ በኩል የሚሰነዘሩ አስተያየቶችንና ቀረርቶዎችን ሁሉ ከግምት በታች ማድረግም ሆነ ከግምት በላይ አድርጎ መመልከት ተገቢ አይደለም፡፡ ምንም እንኳን ግብጽ የምታቀርባቸው የማወዛገቢያ አጀንዳዎች ከላይ በተመለከተው አግባብ መሠረት የሌላቸውና አስቀድመው ምላሽ ያገኙ አጀንዳዎች ቢሆኑም ከብዙ ውትወታ በኋላ በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዘንድ የህዳሴው ግድብን በተመለከተ ቢያንስ ጥርጣሬ ልታሳድር ትችላለች፡፡ ጥርጣሬ ባታሳድር እንኳን ግንባታውን ለማዘግየት የሚያስችላትን እድል ልትፈጥር እንደምትችል መገመትም ተገቢ ነው፡፡ 45 ሺህ ሜጋ ዋት ኃይል የማመንጨት አቅም ያላት ኢትዮጵያ ከአቅሟ በታች ባለችበት ሁኔታና ተፋሰሱን ተከትለው 45 ሚሊዬን ሰዎች እንደሚኖሩ በሚታወቅባት ዓባይ፣ የግብጽ

ድንፋታ ወንዝ የማያሻግር ቢሆንም መላው ኢትዮጵያውያን የዲፕሎማሲያዊው አካል ሊሆኑ ግን ግድ ይላቸዋል፣ ይገባልም፡፡ የዘመኑ ዲፕሎማሲ ከውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ቢሮክራቶች ውጪ ነው፡፡ ምሁራኑ፣ ዲያስፖራው፣ ተቀዋሚ ፓርቲዎችና ሌሎችንም ሁሉ የሚያካትት የዲፕሎማሲ ፍልስፍና መሆኑ ላይ ግልጽ ግንዛቤ ሊይዝም ይገባል፡፡ 500 የሚሆኑ የውጪ ዜጎችን ጨምሮ በአጠቃላይ ሰባት ሺህ የሚሆኑ ሠራተኞች ዛሬ በህዳሴው ግድብ ግንባታ ላይ ሌት ተቀን እየሰሩ መሆኑን ዓለም ሊያውቅልን ይገባል፡፡ የግድቡ ትሩፋትም ለእኛ ብቻ ሳይሆን የተፋሰሱ ሀገራትን ጨምሮ ለበርካታ ሃገራት በተለይም ለግብፅ መሆኑንም ዓለም ያውቅልን ዘንድ ደግመን ደጋግመን ልንጮህ ይገባል፡፡ አይሆንምን ትተሽ ይሆናልን አስቢ የሚለውን የሀገራችንን ተረት ሁሌም እያስታወስን ለግብፅ መወራጨት ትርጉም እየሰጠን መሄድም ይገባናል፡፡ ከዚህ ውጪ ያለው ልዩነት በፍጹም ዋጋ ሊሰጠው አይገባም፡፡ ስለታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ታላቅነትና ጠቃሚነት ለመመስከር ሰው መሆን ብቻ በቂ ነው፡፡

አዎ! ሰው መሆን ብቻ!!! ዛሬ በኒውክሊየር ጣጣ፣ በነዳጅ ተኮር ኢኮኖሚ ውኸቀት ፣ በኢ-ታዳሽ የኃይል ማመንጫዎች እንከን ወዘተ … ለምትታመሰው ዓለማችን፣ እንደ ታላቁ የህዳሴ ግድብ ዓይነት ፕሮጀክቶች እንደ ውድ ሽልማት ሊቆጠሩ እንጂ የውዝግብ መንስዔ ሊሆኑ እንደማይገባ ዓለም ይናገርልን ዘንድ እንጮሃለን፡፡ እንደ ታለቁ የህዳሴ ግድብ ዓይነት ፕሮጀክቶች በየትኛውም መስፈርት ልቆ የሚወጣ የሚተነተንና ሰርክ የሚዘከር ገድል ያላቸው መሆኑንም ዓለም እንዲናገር የቤት ሥራችንን አጠናክረን ልንሰራ ይገባል፡፡

የእኛ ደግሞ በጣም እንደሚለይ ሁሌም በአንድነት ዓለም ይመሰክርልን ዘንድ መሥራትም ጊዜው የሚጠይቀን ጉዳይ ነው፡፡ ለማንም ተደጋግመው በማይነገሩ ምክንያቶች የተነሳ የህዳሴው ግድባችን በጣም ይለያል፡፡ ታላቅነቱ በቁመቱና በስፋቱ አሊያም በሚይዘው የውኃ መጠን ብቻ እንደማይለካ ዓለም ጠንቅቆ ያውቀዋል፡፡

ታላቁ የህዳሴ ግድብ ተዓምራዊ መስታወታችን ነው፡፡ የቆምንበትን፣ የምንሄድበትን፣ ያለፍንበትን፣ የምናስበውን፣ የምናልመውን የምናይበት ሀገራዊ መስታወታችን እንደሆነም ዓለም ያውቅልን ዘንድ እንሻለን፡፡ የህዳሴው ግድብ መልካችን፣ ልካችን በደማቁ የሰፈረበት ውድ ገጻችንም እንደሆነ አውቀው ካልተኙ በስተቀር ግብፀውያንን ጨምሮ መላው ዓለም ያውቃል፡፡ እምቢኝ ብለው ከተኙ ደግመን ደጋግመን ልንቀሰቅሳቸው ይገባል፡፡

እናንተ ግብፃውያን የህዳሴው ግድብ ሃገር የሚያስደንስ ብሔራዊ መዝሙራችን እንደሆነም እወቁት፡፡ ቢነበብ፣ ቢተረክ፣ ቢወሳ፣ ቢሞገስ የማይሰለች፣ በየራዲዮኑ፣ በየቲቪው፣ በየጋዜጣና መጽሄቱ፣ በየስብሰባው፣ በየገበታው፣ በየጫካው፣ በየተራራው ቢወራለት ቢዘመርለት የማይሰለች ጣፋጭ ሀገራዊ እውነታችን ነው፡፡ ታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድባችን!!!